የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ ብራሰልስ
Embassy of The Federal Democratic
Republic of Ethiopia – Brussels

ቀን ;
Date 02/13/2007
ቁጥር ;
Ref. No. BE/CONS/13/504/07

# ማስታወቂያ

## በቤልጂየም፣ ኔዘርላንድና ሉክስምበርግ የምትኖሩ ትውልደ ኢትጵያውያን በሙሉ፣

የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች በትውልድ አገራቸው የተለያዩ የልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ ላይ ከዚህ በፊት የአገልግሎት ክፍያን በማስመልከት የዕድሳት ጊዜ ያለፈባቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ያለቅጣት ለማሳደስ እንዲችሉ እስከ ሐምሌ 30/2007 ዓ.ም መራዘሙ የሚታወቅ ነው።

ይሁንና መረጃው እስከ አሁን ለሁሉም ኢትዮጵያውን ባለመደረሱ ምክንያት መታወቂያቸውን በውቅቱ ያላሳደሱ በመኖራቸው ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጥ ጥያቄ እየቀረበ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት የተወላጅነት መታወቂያው ያለቅጣት እንዲታደስ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ላልተወሰነ ጊዜ መራዘሙን በመግለጽ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ፅ/ቤት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነሐሴ 27 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ብ/መ/ደ/አገ/83/76 በጻፈው ደብዳቤ ለሚሲዮናችን ኣሳውቋል።

ስለሆነም በቤኔሉክስ አገሮች የምትኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆናችሁ በሙሉ በተሸሻለው ውሳኔው መሠረት ከአሁን በፊት የትውልደ ኢትዮጵያ መታወቂያ ካርድ የወሰዳችሁ የተረጋገጠ የልደት ካርድ በማቅረብ የተሰጠው ዕድል መጠቀም እንድትችሉና የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ላልተወሰነ ጊዜ ያለቅጣት ለማሳደስ የተወሰነ መሆኑን እየገለፅን፣ አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላት ማሳደስ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

ኢ.ፌ.ዲ. ሪ. ኤምባሲ ብራሰልስ

Avenue de Tervuren. • 62. • B- 1040 Brussels
Tel. : 00 32 2 771 32 94. • Fax : 00 32 2 771 49 14
Email : etebru@brutele.be
ethio-brussels@MFG..gov.et